## የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት የቦታ ምደባ

### የሕዝብ ያልሆነ ልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ምንድን ነው?

**የሕዝብ ያልሆነ ልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት፣** የግል የሆነ ወይም በግል የሚተዳደር ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት ወይም የትምህርት ክፊለ ጊዜ የሚያቀርብ ነው።

### አንድ ተማሪ የሕዝብ ባልሆነ ትምህርት ቤት መደበኛ የመቆያ ጊዜው ምን ያህል ነው?

የIEP ቡድን አንድ ተማሪ አሁን ባለበት ትምህርት ቤት፤ ከቀድሞው ምደባ የበለጠ ከለላ ባለው የመማሪያ አካባቢ የመቆያ ጊዜውን ይወስናል። በIDEA መሰረት፣ የአንድ ተማሪ ምደባ በትንሹ በዓመት አንድ ጊዜ መገምገም ይኖርበታል፤ በተማሪው IEP ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት፣ እና በተቻለ መጠን ከተማሪው የመኖሪያ ቦታ ቅርብ መሆን አለበት። **አንድ ተማሪን የበለጠ ከለላ ባለው አካባቢ ከሚያስፈልገው ጊዜ የበለጠ ማቆየት የፌደራል ሕግን መጣስ ነው።**

### የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ለተመደቡ ተማሪዎች የLEA ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

እርስዎ (ወላጅ)፣ ተማሪውን በሌላ LEA እንዲገባ ካላደረጉ በስተቀር፤ LEA ከምደባው በፊት፣ በምደባው ጊዜ እና በኋላ፤ ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ለማቅረብ ኃላፊ ነው። ከዚያም፣ አዲሱ LEA፣ ለተማሪው FAPEን የማቅረብ ኃላፊነትን ይወስዳል። ተማሪው የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ሲመደብ፣ የIEP ቡድን የተማሪውን መሻሻል በIEP ሂደት መሰረት አዘውትሮ ለመቆጣጠር ኃላፊ ነው። የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤቱ የIEP ቡድን ስብሰባ ካደረገ፣ LEA በልጅዎ IEP ላይ ለሚደረገው ማንኛውም ውሳኔ፣ እርስዎ እና የIEP ወኪል መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት። የIEP ቡድን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ ተማሪው አነስተኛ ከለላ ወዳለው አካባቢ ሲመለስ፣ ቡድኑ የመዘዋወሪያ እቅድ ማውጣት አለበት።

ተማሪው ወደLEA ለመመለስ ዝግጁ መሆኑን የIEP ቡድኑ ሲያምንበት፣ የLEA እና የሕዝብ ያልሆነ IEP ቡድን አባላት፣ IEPን ለማሻሻል፣ የዝውውሩን እቅድ አስፈላጊነት ለመገምገም እና የIEP ቡድኑ ባወጣቸው የጊዜ ሰሌዳዎች መሠረት መመለሻውን ለመወሰን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

### ልጄ የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ከተመደበ፣ ወላጅ እንደመሆኔ ያሉብኝ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

የልጅዎ IEP ቡድን ዓባል እንደመሆንዎ፣ የእርስዎ ኃላፊነቶች በፊት እንደነበሩ ይቆያሉ፣ ይህም ማለት፤ በልዩ ትምህርት ሂደቶች ውስጥ መካፈልዎን ማረጋገጥ አለብዎት። በተጨማሪም ልጅዎ የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ሲመደብ፣ **ልጅዎ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት በኮሎምብያ ዲስትሪክ LEA መግባቱን** የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብዎት። ልጅዎ በሆነ ምክንያት በተዘጋ የቻርተር LEA ውስጥ ተመድቦ ከሆነ፣ ልጅዎን በሌላ LEA ማስገባት አለብዎት። ልጅዎ ከሚማርበት ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለመቀጠል ዕድሜው/ዋ ካለፈም በዚሁ ውስጥ ይካተታል።

---

**ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን የሚከተለውን ያነጋግሩ፡**

**Office of the State Superintendent of Education**
**Division of Special Education**
1050 First Street, NE 5th
Floor Washington, DC 20002
ስልክ: (202) 727-6436/ ፋክስ: (202) 299-2135

OSSE ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን ለOSSE ፕሮግራሞችና ግልጋሎቶች እኩል የሆነ ዕድል ይሰጣል። OSSE አማራጭ አቀራረብ ያላቸው የፅሁፍ ማስታወቂያዎችን፣ የስብሰባ/የቀጠሮ ቀን ቃለ ጉባኤዎችን፣ አነስተኛ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን፤ የምልክት ቋንቋ የማስተርጎም ግልጋሎትን ጨምሮ ያቀርባል። የምልክት ቋንቋ የማስተርጎም ግልጋሎት ካስፈለገ፣ በOSSE ወይንም በOSSE ዝግጅት ከመካፈልዎ በትንሹ ከ5 የስራ ቀናት በፊት ለዚህ ግልጋሎት ብቃት ያለው ግለሰብ እንዲመደብልዎት ጥያቄዎን ለOSSE ADA አስተናባሪ ማስገባት አለብዎት። የOSSE ADA አስተናባሪ ወ/ሮ ጆስሊን ጆንሰን ናቸው። በስልክ ቁጥር (202) 724-2134 ወይንም በኢሜል jocelyn.johnson@dc.gov. ይገኛሉ።

# የምደ ቦታ ግምገማ ፖሊሲዎችና ክንውኖች፣ የታረመ

*የወላጅ የፅሁፍ ማስታወቂያ*

**መግቢያ:** ጥር 5 ቀን 2010 ዓ.ም. የግዛቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ - የልዩ ችሎታ ትምህርት ክፍል (OSSE DSE) "የተሻሻለ የቦታ ግምገማ ፖሊሲና ክንውኖች (PPPR)" አቀረበ። ይህ ፖሊሲ እያንዳንዱን ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ከLEA ውጪ የበለጠ ከለላ ወዳለው የቦታ ለውጥ ማድረግ የሚያስብ የአካባቢ የትምህርት ድርጅት (LEA) ሚና እና ኃላፊነቶችን ያብራራል። የዚህ የወላጅ የፅሁፍ ማስታወቂያ ጥቅሙ፣ ስለ ቦታ ምደባ ግምገማ ሂደትና ወላጅ ስለሚኖረው ኃላፊነት ተጨማሪ መረጃዎችን መስጠት ነው።

**ማስታወሻ፡** OSSE የግዛቱ የትምህርት ድርጅት እንደመሆኑ፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ማንኛውንም የፌደራልና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህግጋትና ደንቦች ማክበር ይገባዋል። እንደዚሁም OSSE ለቦታ ምደባ ክንውኑ በሚደረገው ክትትል የሚያጋጥሙ ማንኛውንም ነገሮች አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

## ዝቅተኛ ከለላ ያለው አካባቢ (LRE) ምደባ

### IEP ምንድን ነው?

**IEP፣** ወይም ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም፣ ከእርስዎ (ከወላጅ)፣ አጠቃላይ አስተማሪዎች፣ የልዩ የትምህርት አስተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ ልጁ (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) እና ሌሎች በልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ግለሰቦች፤ በትምህርት ቤቱ የልጅዎን የትምህርት መሻሻልና ለእርሱ/ሷ ስኬት እርዳታ በህብረት ለመስጠት የተዘጋጀ እቅድ ነው። ይህ ቡድን የIEP ቡድን በመባል ይታወቃል።


### ምደባ ምንድን ነው?

**ምደባ፣** ከልዩ ትምህርት ጋር ባለው ግንኙነት መሰረት፣ የግልጋሎቶቹ ደረጃና ቡድኑ ለልጅዎ ስኬታማነት አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምነው የአካባቢ ዓይነት ነው። ምደባ፣ በዚህ የቃል አገባብ፣ ቦታን **<u>አያመለክትም</u>** (ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን ቦታ ወይም ልጅዎ ስርዓተ ትምህርቱን የሚወስድበትን ህንፃ)።

### ዝቅተኛ ከለላ ያለው አካባቢ (LRE) ምንድን ነው?

በፌደራል ሕጉ መሠረት (የአካል ጉዳተኞች ትምህርት እንቅስቃሴ ድንጋጌ፣ ወይም IDEA) በተቻለ መጠን፣ ሁሉም የሕዝብ ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች ልጆች የአካል ጉዳት ከሌላቸው ጋር  መማራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።  ልዩ ትምህርት አሰጣጥ፣ ልዩ ክፍሎች፣ ወይም የአካል ጉዳተኞች ተማሪዎችን ከአጠቃላይ የትምህርት ስርዓት አካባቢ ማግለል ሊፈጠር የሚችለው የአካል ጉዳተኝነቱ  እጅግ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ትምህርት አሰጣጡ በተለመዱት ክፍሎች ውስጥ ከተጨማሪ እርዳታ እና ግልጋሎቶች ጋር በተሟላ ሁኔታ ሊካሄድ ካልቻለ **<u>ብቻ</u>** ነው።  በነኚህ ሁሉ ሁኔታዎች የIEP ቡድን ለተማሪው ምን አይነት አካባቢ አመቺ እንደሚሆን የሚወስን ይሆናል። የሚከተለው በስራ ላይ ያለው አማራጭ የምደባ መለኪያ ነው፡

#### ዝቅተኛ ከለላ ያለው አካባቢ መለኪያ




## የምደባ ውሳኔ

### የምደባ ውሳኔ በሚደረግበት ጊዜ፣ ቡድኑ ማድረግ ያለበት...

- የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት በIEP እቅድ ሂደት መወሰን።
- በIEP የተማሪዎች ፍላጎት ላይ ስምምነት ከተደረሰና ከምዝገባ በኋላ፣ የምደባውን አማራጮች በLRE መለኪያ (በግራ በኩል ያለውን ስዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ)  ላይ በደረጃ እንደተመለከተው ከዝቅተኛ ከለላ እስከ ከፍተኛ ከለላ አካባቢ መገምገም።
- የሚከተሉትን ሶስት እውነታዎች በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ መመልከትና መነጋገር፡፡
    1. ከመረጃ ክምችት የተገኙ መረጃዎች (ለምሳሌ፡ ግምገማዎች፣ የሂደት ሪፖርቶች፣ አስተያየቶች፣ ወዘተ...) ተማሪው ከሚከተሉት አንዱ ወይም ሁለቱ አጠቃላይ የትምህርት አቀማመጥ ሊገለገልበት እንደሚችል ማጤን፡ (<u>ማስታወሻ፡</u> የሚከተለው ዝርዝር ሁሉንም ያካተተ አይደለም)
        - ፕሮግራም እና/ወይም መርሃ ትምህርትን ማስማሚያዎች ወይም ማስተካከያዎች
        - በልዩ ትምህርትና በጠቅላላ ትምህርት መምህራን መካከል ትብብር
        - ተጨማሪ እርዳታዎችና እገዛዎች
        - አጋዥ ቴክኖሎጂን መጠቀም
        - ውጤታማ በሆነ ግምገማ የስነምግባር ጣልቃ ገባነት እቅድ መፍጠርና በተግባር ላይ ማዋል።
    2. ለLRE የተሰጠውን ጥቅማ ጥቅም ከፍተኛ ከለላ ከተሰጣቸው አካባቢዎች ጋር ማወዳደር። (**<u>አስታውሱ፡</u>** በጠቅላላ ትምህርት አቀማመጥ የሚደረገው ምደባ በተማሪው አንድ አይነት ነገሮችን በተመሳሳይ መንገድ የመማር ችሎታ ላይ የተመረኮዘ አይደለም።)
    3. እያንዳንዱን የምደባ አማራጭ ሊያስከትል የሚችለውን ጠቀሜታ ወይንም ጉዳት፤ የሎጅክ ለውጦችን፣ እንደ ከቤት ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት የመጓጓዣ ሁኔታዎችን ጨምሮ ግምት ውስጥ ማስገባት (ለምሳሌ፣ ርቀትና የመጓጓዣ ጊዜ)።
- ቡድኑ ተማሪውከLEA ውጪ ግልጋሎቶች እንዲቀበል ከተስማማ፣ የIEP ቡድኑ ለተማሪው አነስተኛ ከለላ ወዳለው አካባቢ እንዲመለስ የመዘዋወሪያ እቅድ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የIEP ቡድኑ ይወስናል።

### ወላጆች በምደባ ሂደቱ ላይ ለምን ይጠቅማሉ?

- የወላጆች ተሳትፎ ለተማሪዎች ስኬታማነት ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ተመራማሪዎች ያሳያሉ። ወላጆች ለልጆቻቸው የወጤታማነት ገደብ በማስቀመጥ እና በትምህርት ቤትና በቤት ውስጥ በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ያበረታቷቸውል።
- ወላጆች ልጆቻቸውን በሚገባ ስለሚያውቋቸው ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለእቅዱ ሂደት ሊያቀርቡ ይችላሉ። ስለልጅዎ የሚያውቁትን ለ IEP ቡድን ሊረዳና ከልጅዎ ትክክለኛ አካባቢ ጋር የሚሰራ IEP ለመፍጠር ይረዳል።
- በወላጆችና በአስተማሪዎች መካከል የሚደረገው ትብብር በጠቅላላ የIEP የእቅድ ሂደት ላይ ለእያንዳንዱ ተማሪ ጠቃሚ የትምህርት ውሳኔዎችን ለማድረግ ይረዳል።
- ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት እውነታዎች በተጨማሪም፣ የፌደራል ሕጉ ወላጆች ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይጠይቃል።

### ስለዚህ ወላጅ እንደመሆኔ ምን ማድረግ አለብኝ?

- **ተሳታፊ መሆንዎን ይቀጥሉ!** የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ፣ በሁሉም የልዩ ትምህርት ሂደት ክፍሎች መሳተፍ፤ ስብሰባዎች ላይ መገኘትንና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትም ላይ መሳተፍ ይገባዎታል። ተሳታፊ መሆንዎ ለልጅዎ የትምህርት ስኬት እጅግ ጠቃሚ ነው።